# መኢሶን የተከተለው የትግል ታክቲክና የ1966 ዓ/ም የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት

በኢትዮጵያ በየካቲት ወር የ1966 ዓ/ም አብዮት ከፈነዳ እነሆ አርባ ዓመት ሊሆነው የቀረው ሦስት ወር ብቻ ነው ። ታዲያ ስለዘመኑ አሁን ውይይት መደረግ መጀመሩ እንዴት ያበረታታል ። በቅርቡ ከሕይወት ተፈራና " TOWER IN THE SKY " ብላ የሰየመችውና ፣ ከካሕሳይ አብርሃ ደግሞ " የአሲምባ ፍቅር " ብሎ የሰየመው መጻሐፎቻቸው ታትመው ለውይይት መነሻነት መብቃታቸው እጅግ ግሉህ ጠቀሜታ አላቸው ። እስካሁን ስሜታዊነት በፈጠረው ውዥንብርና ስለወቅቱም ጥርት ያለ አመለካከት እንዳይኖር አውቀው የሚያድበሰብሱ ምሁራንም በመጨመራቸው ፤ በዛን ወቅት ምን እንደተካሔደ ጥርት ያለ ግንዛቤ በተለይ ወጣቱ ተውልድ እንዳይኖረው አድርጓል ። የሕይወት መጻሐፍ በአማርኛ ቀርቦ ቢሆን ኖሮ ጠቀሜታው የጎላ በሆነ ነበር ። የውይይቱ ጠቀሜታ የሚጎላው ደግሞ የ1966 አብዮት ካነሣቸው ቁልፍ ፖለቲካዊ ጥያቄዎች አሁንም ድረስ በቂ መልስ ያላገኙ መሆኑ ነው ። አንዳንድ ነገሮች አለቀላቸው ይባልና እንደገና በሆነ መልኩ አንሠራርተው ብቅ ይላሉ ። እኔም የዚህን የውይይት ፈለግ በመከተል በኢትዮጵያ አብዮት ወቅት መኢሶን ስለተከተለው የትግል ታክቲክ አንዳንድ ነገሮችን ለመሰንዘር ወሰንኩ ። በየካቲት ወር 1966 ዓ/ም በኢትዮጵያ የተቀሰቀሰው አብዮት ከሞላ ጎደል በተራማጆች በኩል ያልተጠበቀ አልነበረም ። ምክኒያቱም በዛን ወቅት ዓለም በካፒታሊስቱና በሶሻሊስቱ የኢኮኖሚ ሥርዐት ለሁለት ጎራ ተከፍላ የተለያዩ ትግሎች የሚካሔዱባት መድረክ ነበረች ። የተወሰኑት አገሮች ከምዕራቡ ዓለም ቅኝ ግዛት ነፃ ለመውጣት ትግል ሲያደርጉ ፣ ሌሎቹ ደግሞ የራሣቸውን ጨቋኝ ገዥዎች በማስወገድ አገራቸውን ከእጅ አዙር ቅኝ-አገዛዝ አላቀው ፣ ሕዝባዊ ሥርዐት በምትኩ ለማቋቋም የሚንቀሳቀሱበት ወቅት ነበር ። የኢትዮጵያ ተራማጆችም በ1953 ዓ/ም በተሞከረው መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ተነቃቅተው ፣ ከ1959 ዓ/ም አንስቶ በይፋ ለሥርዐቱ (ለባለባቱ) ስር-ነቀል ለውጥ መንቀሣቀስ የጀመሩበት ወቅት ነበር ። እስከዚያ ወቅት ድረስ ግን በተለይ የተማሪው እንቅስቃሴ ሲጠይቅ የነበረው ጥገናዊ ለውጥን ነበረ ። የባላባቱ ሥርዐት ግን ለዚሁም በቂ ሆኖ አልተገኘም ። በተለይ ወደኋላ ላይ ፣ ከፊሉ የተማረው ክፍል ትምህርቱን እንደጨረሰ ሥርዐቱን ለማገልገል ወደ ሀገር ቤት ከመምጣት ፋንታ በውጭ አገር ተደራጅቶ በቋሚነት የሥርዐቱን ምንነት ማጋለጥ መጀመሩ ፣ በአገር ቤት ያሉትንና ከአገር ውጭ ይገኙ የነበሩ ኢትዮጵያዊያንን ንቃተ-ሕሊና በተወሰነም ደረጃ ቢሆን ከፍ ለማድረግ በቅቷል ።

አገሪቱም በምዕራቡ ዓለም የኢኮኖሚ ሥርዐት ምህዋር ውስጥ ስትሽከረከር መቆየቷ ፣ የወሎና የትግራይን እርሀብ አተረፈላት እንጂ ሌላ ጥቅም እንዳላስገኘላት ምሁራኑ ተገነዘቡ ። ስለዚህም ምሁራኑ ከዚህ ተውሳክ ከሆነ ሥርዐተ ኢኮኖሚ አገሪቷን ማላቀቅ ግድ አላቸው ። ለዚሁም ችግር መፍቻ ይሆናል ተብሎ ደግሞ ፣ የሶሻሊስቱ ሥርዐተ-ኢኮኖሚ እንደ አማራጭ ተወሰደ ። እንግዲህ የ1966ቱ የየካቲት ሕዝባዊ አመፅ የተቀሰቀሰው አብዛኛው የተማረው ክፍል ይህንን አቋም ከወሰደ በኋላ ነበር ማለት ይቻላል ። እርግጥ ነው የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ልማትን በተመለከተ የምዕራቡ ዓለም አሉታዊ ተፅዕኖ ቢኖርበትም ቅሉ ፤ በአገሪቷ ዘመናዊ ትምህርትን በማይናቅ ደረጃ አስፋፍቷል ፤ አንዳንድ መሠረተ ልማቶችን መገንባቱም አሌ የሚባል አይደለም ። ዘመናዊ የመከላከያና የሲቪል ተቋሞችን አቋቁሟል ። ተቋሞቹም በራስ ዜጋ እንዲመሩም አድርጓል ። በውጭ ፖሊሲውም የአፍሪካ ሕብረትንና የአፍሪካ ሕዝቦች ፀረ-ቅኝ ግዛት ትግልን በመደግፍ ተንቀሳቅሷል ። በተለይ ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት መቋቋም ትልቅ አስተዋፆ አድርጓል ። ሆኖም ግን ሥርዐቱ ያረጀና ያፈጀ በመሆኑ የተነሣ ፣ በአገር ውስጥ ፣በገጠርም ሆነ በከተማ አንዳንድ ትግሎች በመካሔድ ላይ ነበሩ ። በወቅቱ ለሥርዐት ለውጥ የሚታገሉ የሕብረተ-ሰብ ክፍሎች እንደመኖራቸው መጠን ሁሉ ፣ ከአገሪቷ ግዛት ቆርሶ ለመውሰድና ከግዛቱ ለመገንጠል የሚካሔዱም ትግሎች ነበሩ ። በኋላም ላይ አብዮቱን ውስብስብ ያደረጉት እነዚህ ኃይሎች መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል ። ከተገንጣዮቹም ጀርባ ሆነው ኢትዮጵያን ወደብ አልባ በማድረግ ከቀይ ባሕር ለማራቅ የሚንቀሳቀሱም አንዳንድ የአረብ ማህበረ-ሰቦች እንደነበሩ በአሁኑ ወቅት ለአብዛኛዎቻችን የተሰወረ አይመስለኝም ።

በወቅቱ በሕብረተ-ሰቡ ንቃተ-ህሊና ላይ የማይናቅ ተፅዕኖ አሳድሮ የነበረው የተራማጁ ክፍል አስተሳሰብ ነበር ቢባል ከዕውነት የራቀ አይመስለኝም ። መለዮ ለባሹም የሕብረተ-ሰቡ አካል እንደመሆኑ መጠን ፣ የግራው ኃይል አስተሳሰብ ወደርሱም ሠርፆ መግባቱ አልቀረም ። እንግዲህ ይኸንን ውጥንቅጥ ሁኔታ የተረዳው መኢሶን "ውሻ በቀደደው ፣ ጅብ ይገባል" ይባላልና ፤ ይህ እንዳይሆን በትግሉ ወቅት ብርቱ ጥንቃቄን ማድረግ ነበረበት ። ስለዚህ በሕዝባዊ አመፁ ወቅት ግዛት ገንጥሎ ለመውሰድ ካሰፈሰፈው የሱማሌ መንግሥትና ለጠባብ ጥቅማቸው በማሰብ ከግዛቷ ተገንጥለው ለመውጣት አመቺ ጊዜን ሲጠባበቁ ከነበሩት ከሻዕቢያና ከጀበሐ የኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነቱን ጠብቆ ባላባታዊውን ሥርዐት እንዲታገልና ፣ ዲሞክራሲያዊ ሥርዐትን ለመገንባት ይችል ዘንድ የሚያበቃውን የትግል ሥልት መቀየስ ነበረበት ። ሆኖም ግን ለኢትዮጵያ መድህን ይሆናል ብለን ያቋቋምነው ድርጅት (ኢሕአፓ) ፣ ገና በጨቅላነቱ ተገንጣዮቹ ጠልፈው በመውሰድ በሥራቸው በማደራጀታቸው የተነሣ ፣ ለመኢሶን ትግሉን የባሰ ውስብስብ አድርጎበት እንደነበር ፀሐይ የሞቀው ሀቅ ነው ።

የመንግሥትን ሥልጣን የጨበጠው ኃይል ሁሉንም ነገር መወሰን ስለሚችል ፣ የማንኛውም አብዮት ቀዳሚው ጥያቄ የሥልጣን ጥያቄ ይሆናል ። መኢሶንም ይኼንን ጥያቄ በተመለከተ በውስጡ ተፈጥሮ የነበረውን ልዩነት በቅድሚያ በዲሞክራሲያዊ መንገድ በውይይት ከፈታ በኋላ ፣ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት የሚለውን ማታገያ መፈክር አውርዶ ፣ ሥልጣን ወደ ሕዝብ የሚሸጋገርበትን መንገድ በተመለከተ "ብሔራዊ አብዮታዊ ዲሞክራቲክ አብዮት" ፕሮግራም ላይ ቁልጭ አድርጎ ያስቀምጣል ። ሕዝባዊ ሥልጣን ሊመጣ የሚችለው ፣ የሠፊው ኢትዮጵያ ሕዝብን ይሁንታ በምርጫ ሲያገኝ ብቻ መሆኑን በማያሻማ መልኩ ፕሮግራሙ ላይ እንዲህ ሲል አስፍሮታል ። **" የሠፊው ሕዝብ ትግል ተደራጅቶና ገፍቶ አብዮታዊ ሕዝባዊ ግንባሩ እንደተቋቋመ በትግሉ ውስጥ የተሳተፉት የግንባሩ አባል ፓርቲዎችና የፖለቲካ ድርጅቶች ከሚያቀርቧቸው ምልምሎች መሀከል ሕዝቡ በሙሉ ነፃና ምሥጥራዊ በሆነ ምርጫ እንደራሴዎቹን መርጦ የመንግሥቱን ከፍተኛ ሥልጣን ወደሚይዘው አብዮታዊ ሸንጎ ይልካል ። የሕዝቡ ወኪሎች አጥንተው ባፀደቁት ሕገ-መንግሥት መሠረት የመንግሥቱ መዋቅሮች ፤ ዘርፎችና የሥልጣን ክፍፍሎች ተወስነው በወዝ-አደሩ ፓርቲ መሪነት ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ይቋቋማል ።"** ደርጉም ቀደም ሲል አውጆት የነበረውን የኢትዮጵያ ሶሻሊዝምን እርግፍ አድርጎ በመተው መኢሶን ከሌሎች ተራማጆች ጋር በመሆን ያቀረበውን የብሔራዊ አብዮታዊ ዲሞክራቲክ ፕሮግራምን ተግባራዊ ለማድረግ ቃል ከገባ በኋላ ፣ በትብብር መሥራት ተጀመረ ። የመንግሥት ሥልጣን የጨበጠው አካል መኢሶን ላቀረበው ፕሮግራም ተግባራዊነት እታገላለሁ ማለቱ ለመኢሶን ጥሩ አጋጣሚ ነበር ማለት ይቻላል ። በወጣት መኮንኖችና በባለሌላ ማዕረጎች የተቋቋመው መንግሥት ደግሞ ከባላበቱ ሥርዐት ገዥ መደብ ጋር ምንም ዐይነት የጥቅም ግንኙነት ያለመኖሩ ሁኔታ ፣ የሥርዐት ለውጡን ለማምጣት አመቺ ሁኔታን ፈጥሮ እንደነበር ግልፅ ነው ። መኢሶንና ስብስቡ የራሱን በነፃነት የመሥራት መብቱን በአዋጅ ካስጠበቀ በኋላ ፣ ከደርጉ ጋር በሕብረት የባላባቱን ሥርዐት ለማስወገድ መታገሉን ተያያዘው ።

በነገራችን ላይ መኢሶን ከደርግ ጋር ተባብሮ ሠራ ይባላል እንጂ ፤ እንደ ዕውነቱ ከሆነ ግን ደርግ ነው ከመኢሶን ጋር ተባብሮ የሠራው ። እንዴት ቢባል ፣ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ከተቋቋመ በኋላ ፣ ደርግ ሲታገል የነበረው የራሱ የነበረውን የኢትዮጵያ ሶሻሊዝምን ፕሮግራም ተግባራዊ ለማድረግ ሳይሆን ፣ በመኢሶን የቀረበለትን ፕሮግራም ተግባራዊ ለማድረግ በመሆኑ ነው ። በወቅቱ በመኢሶን የቀረበው ፕሮግራም የሚያመለክተው የሥልጣን ሽግግርን መንገድ ብቻ ሣይሆን ፣ የአብዮቱ ወዳጆችና ጠላቶች እነማን እንደሆኑም በተጨማሪ በግልጽ ያመለክታል ። ይህ ማለት ደግሞ መኢሶን በወቅቱ የፖለቲካ አካሔዱ በመደቦች ባህሪ ትንታኔና በቅራኔዎች አፈታት ሕግጋት ላይ የሚመራ ነበር ማለት ነው ። ከዚህ ትንታኔ በመነሣትም መኢሶን ወታደራዊው ደርግ የመጀመሪያውን የአብዮት ደረጃ ከሠፊው ሕዝብ ጋር አብሮ ለመጓዝ ይቻል እንጂ ፣ ደርጉ የንዑስ ከበርቴ ስብስብ እንደመሆኑ መጠን አብዮቱን ወደ ሁለተኛው ደረጃ እንደማያሸጋግረው መኢሶን ጠንቅቆ ያውቅ ነበር ። በዚህ ረገድም ሠፊው ሕዝብ ለአፍታም እነዳይዘናጋ ፣ይኼንኑ ሀቅ በሚያዚያ ወር 1968 ዓ/ም ለሕዝብ በይፋ ባወጣው ፕሮግራሙ ላይ ፤ " ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት ይህን ፕሮግራም ከሥራ ላይ ሊያውል አይችልም ። ስለዚህም ደርጉ የቀድሞ ወላዋይነቱን ካስቀረ ፤ የዚህን መለስተኛ አዋጅ ሥራ ላይ መዋል የሚያግዙ እርምጃዎች በመውሰድ የሠፊውን ሕዝብ ትግል ሊያገለግል ይችላል ። ሠፊውን ሕዝብ ተክቶ ግን ይህን ፕሮግራም ከሥራ ላይ ሊያውል አይችልም ። የዚህ መለስተኛ ፕሮግራም ታሪካዊ ቦታ

ለአገራችን ችግሮች ዛሬውኑ መፍትሔ ስለሚያስገኝ አይደለም ፡፡ ሠፊው ሕዝብ ለነዚህ መፍትሔዎች ራሱ እንዲታገል ለማንቃት ፣ ለማደራጀትና ለማስታጠቅ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር በመሆኑ ነው ፡፡" ሲል ገልፆታል ፡፡

በየጊዜው በሚያወጣቸው ልሳኑ ላይም ይኼንኑ ከመወትወት አልቦዘነም ፡፡ ለምሣሌ ሐምሌ 1968 የወጣው የሠፊው ሕዝብ ድምፅ ቁጥር 43ን ብንመለከት ፣ " ዕውነተኛ ሕዝባዊ አብዮት እረጅምና መራራ ነው ፡፡ በዚህም እረጅም አብዮታዊ ጉዞ መንገዱን አብሮ የጀመረ ሁሉ አብሮ አይጨርስም ፡፡ " ሲል በትግሉ ወቅት የመደብ ሽግሽግ ሊኖር እንደሚችል ያመለክታል ፡፡ ጥር 30 ፣ 1969 ዓ/ም ያወጣውን ሰህድ ቁጥር 50 ን ብንመለከት ደግሞ ፣ "የኢትዮጵያ መለዮ ለባሽና ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ለአብዮቱ እስካሁን ያደረጉት አስተዋፆ በጣም ከፍተኛ መሆኑንና ወደፊትም ብዙ ሊያበረክቱ እንደሚችሉ ቢያምኑም ፣ እነዚህ ኃይሎች እንዳሉ እስከ መጨረሻው ለአብዮቱ ይቆማሉ በሚለው የሕልም እንጀራ ድርጅታችን ፈጽሞ አያምንበትም ፡፡ በደርጉ ውስጥም ሆነ በመለዮ ለባሹ ውስጥ ያሉት አብዮታዊና ፀረ-አብዮታዊ ኃይሎች ሠልፋቸውን ለይተው የሚጠፋፋበት ወቅት በእርግጥ ይመጣል። ለዚህም ነው ፣ የኢትዮጵያ ሠፊ ሕዝብ በየእለቱ ይበልጥ መንቃት ፣ መደራጀትና መታጠቅ ያለበት ፡፡ " በማለት ያስጠነቅቃል ፡፡ ደርጉ የብሔራዊ አብዮታዊ ዲሞክራቲክ አብዮትን ፕሮግራም በይፋ ከማወጁ በፊት ፣ መኢሶን የራሱን ፕሮግራም ለሕዝብ በይፋ ባሣወቀበት ወቅት ፣ ፕሮግራሙን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ፣ መኢሶን ያላንዳች ማወላወል ፣ በሚሥጢርና በይፋ ፣ በሕጋዊ መንገድና በሕገ-ወጥነት ፣ በሠላማዊ መንገድና በአመፅ ፣ እንደጊዜውና እንደሁኔታው በሚለወጥ ታክቲክ ፣ ምንም ጊዜና ምንም ሁኔታ በማይለውጠው ቆራጥነትና ታታሪነት የሚታገሉ አብዮታውያንን አስተባብሮ ለኢትዮጵያ ሠፊ ሕዝብ ነፃነትና አንድነት ማሰለፉን ገልፆ ነበር። መኢሶን ይኼንን ተለዋዋጭ የትግል ስልት መከተል የተገደደው ደርጉ በትግሉ ውስጥ በዘላቂነት የመቆየቱ ጥያቄ ላይ በነበረው አቋም የተነሣ መሆኑ ግልፅ ነው ፡፡ በትግሉ ወቅት መኢሶን በዋናነት ከአብዮቱ ዋና ጠላቶች ጋር ቢጋፈጥም ቅሉ ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ደርጉ የሚወስዳቸውን የተሣሣቱ እርምጃዎች እንዲያርም አበክሮ መታገሉን ያቆመበት ጊዜ አልነበረም ፡፡ ይህም ሁኔታ መኢሶን የነበረውን ውሱን የሠለጠነ የሰው ኃይል ለራሱ ሣይቆጥብ በሕጋዊ መድረክ ላይ እንዲያሰማራ የግድ አለ ፡፡ ይኼውም መኢሶንን የኋላ ኋላ በጣም ጎድቶታል ፡፡ የመኢሶን አብዮታዊ ጥረት የአብዮቱን ጎራ አጠናክሮት እንደነበር ጠላቶቹም ያውቁታል ፡፡ ሆኖም ግን ጠላቶቹ መኢሶን የአብዮቱን ጎራ አጠናከረ ከማለት ፋንታ ፣ ደርግን አጠናከረ ማለትን ይመርጣሉ ፡፡ ደርግ መኢሶን እንደ ተነበየው ከዚህ በኋላ በአብዮቱ መግፋት "የራሴን መቃብር እንደመቆፈር ይሆንብኛል" በማለት ፣ በተለይ የኢሕአፓ አባልና ደጋፊ የነበሩት እነ ሻምበል ሞገስና ዓለማየሁ ኃይሌን የመሣሰሉት የደርግ አባሎች ጥር 26 ቀን ፣ 1969 ዓ/ም በነመንግሥቱ ኃይለማርያም ከተገደሉ በኋላና ፣ እነመንግሥቱም ከሶቭየት ሕብረት ጋራ ግንኙነታቸውን ካጠናከሩ በኋላ ፣ ሥልጣን ለሕዝብ ለቅቄ ወደ ጦር ካምፓችን እንመለሳለን ብለው በአዋጅ ለሕዝብ የገቡትን ቃል-ኪዳን ወደ ጎን በማለት ያለሕዝብ ይሁንታ ሥልጣን መቆናጠጥ ፈለጉ ፡፡ በዚህን ወቅት መኢሶን ለነመግሥቱ እርኩስ እቅድ አባሪ ተባባሪ ባለመሆን በሕዝብ ጎን እንደወትሮው በፅናት ቆመ ፡፡ ሥልጣንን በተመለከተ መኢሶን በወሰደው አቋም የተለያዩ ሰዎች መኢሶንን ኮንነውታል ፡፡ ለምሣሌ አቶ ተስፋዬ መኮንን ጥቅምት 1985 "ይድረስ ለባለታሪኩ" ብለው በሠየሙት መጸሐፋቸው ገጽ 243 ላይ ፣ " …በዚህም ሕብረቱ በአስቸኳይ መዋሀድና አመራሩን መሸከም ካልቻለ በቀር የደርግ አመራር ሊቋቋመው የማይችለው አስፈሪ የሆነ የተቀነባበረ የወረራና የመገንጠል ጦርነት የመጣ እንደሆነ ጭንቀት በተሞላው ሁኔታ በኮል/መንግሥቱ መገለፁን ዛሬ በአቋም ስለተለያየን መካድ አይቻልም ፡፡ ለዚህ ግን አለመሳካት ምክኒያቱ የመኢሶን ወደኋላ ማፈግፈግ ነበር ፡፡" ሲሉ መኢሶንን ያማርራሉ ፡፡ (ሠረዝ የራሴ) ዘነበ ፈለቀም "ነበር" ብለው በሠየሙት መጸሐፋቸው ገጽ 270 ላይ ፣ "በዚያን ወቅት ኢማሌድህን "አመራሩን ተረከብ " አሉት ፡፡ " አልችልም እንደገባህበት አንተው ተወጣው " እንደማለት አፈገፈገ ፡፡" በማለት መኢሶን ኃላፊነትን እንደሸሸ አድርገው ያቀርቡታል ፡፡ መኢሶን ግን የሥልጣን ሽግግርን በተመለከተ አቋሙን ቀደም ሲል በግልፅ ብሔራዊ አብዮታዊ ዲሞክራቲክ ፕሮግራሙ ላይ እንዳስቀመጠ ይታወቃል ፡፡ እነዚህ መኢሶንን ከሥልጣን ሸሸ ብለው ይውቀሱት እንጂ ፣ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ደግሞ "**ሥልጣን ፣ ባህልና አገዛዝ ፣ ፖለቲካና ምርጫ**" ብለው በ2003 ባሳተሙት መጸሐፋቸው ገጽ 39 ላይ ፣ " ደርግ ማለት በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ከሕዝቡ ጋር የኖሩ ፣ አገሩንና ሕዝቡን የሚያውቁ መለዮ ለባሾችን የያዘ ሲሆን በሕዝብ ድርጅት ውስጥ የገቡት ዋና ዋናዎቹ ደግሞ በፈረንጅ አገር ሲኖሩ የነበሩና "በአብዮቱ" ለማትረፍ ተጠራርተው የመጡ ነበሩ ፣ " ደም !ደም !" እያሉ ደርግን ወደ ግድያ ሲገፋፉት የነበሩት እነዚሁ "አብዮተኞች" ናቸው ፣ እንዲህ በፈረንጅ አገር ታሪክና አስተሳሰብ በተወጠሩ **የሥልጣን ጥመኞች** ግፊት የደርግ ግፍ ዳር እስከ ዳር የኢትዮጵያን ሕዝብ በሙሉ ነካ ፡፡ " ሲሉ ወታደሩን የኢላማ ተኩስ አስተማሩ እንደማለት ዐይነት ክስ ይከሱናል ፡፡ እነዚህን ለጊዜው እንተዋቸውና ወደ ደርጉ እንመለስ ፡፡ መኢሶን ደርጉ ከአብዮቱ ማፈግፈጉን በተገነዘበበት ጊዜ ፣ ቀደም ሲል ለሕዝቡ ቃል በገባው መሠረት የትግል ሥልት ለውጥ በማድረግ በሕቡዕ መታገል ይጀምራል ፡፡ ደርጉም ሕዝቡን የሚያነቃውንና የሚያደራጀውን መኢሶንን ለሥልጣን ጥሙ ሲል ፣ ከፖለቲካ መድረኩ በመግደልና በማሰር በማግለሉ ፣ እነሻዐቢያ በኢሕአፓ በኩል ሞክረውት ያልተሳካላቸውን ፣ ደርግ አሳካላቸው ፡፡ በመጨረሻም መንገዱ ጠፍቶበት ሲደናበር እርሱም ተንኮታኩቶ አገሪቷንም ወደ አዘቅት አወረዳት ፡፡ ለዛሬ በዚሁ ላብቃ ፡፡

መርዕድ ከበደ

ሎሚ መፅሄት ቅፅ 3 ቁጥር 77 ጥቅምት 2006